ኢትዮጵያ - ጫት (አነቃቂ እጽዋት) - የህፃናት የጉልበት ሥራ

ዕድሜያቸው ከ 8 እስከ 17 የሆኑ ሕፃናት ኢትዮጵያ ውስጥ በ*ጫት*ምርት ላይ እንደተሰማሩ መረጃዎች ያሳያሉ። በ2017 (2009/8) በተደረገ ጥናት መሠረት በወንዶ ገነት ቹኮ ከተማ እና በምስራቅ ሀረርጌ በአወዳይ ከሚገኙ ጫት ሰራተኞች መካከል ከ 50 በመቶ እስከ 70 በመቶ የሚሆኑት ልጆች ናቸው። አወዳይ ውስጥ 5,000 የሚሆኑ ሕፃናት ከንግዱ ጋር የተገናኙ መሆናቸው የሚገመት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በግምት 2,000 የሚሆኑት ዕድሜያቸው ከ 15 በታች ነው። ምንም እንኳን *ጫት (ካታ ኤዱሊስ)* ኢትዮጵያ ውስጥ በሕግ የሚፈቀድ ሲሆን ዕፅዋቱ በጣም ከፍተኛ ሱስ የሚያስይዙ ማዕከላዊ የነርቭ ትስስርን የሚያነቃቁ - ካቲኖን እና ካቲን - የሚባሉትን ንጥረ ነገሮች በመልቀቁ የረጅም ጊዜ የነርቭ ጎዳቶችን ጨምሮ  በጫቱ ምክንያት የሚመጣ የስነ-ልቦና ችግርን ይፈጥራል። ጫትን በማብቀል፣ በመግረዝ እና በመጠቅለል ተግባር ላይ የተሰማሩ ሕፃናት ከተክሉ ጋር በመገናኘታቸው የዕፁ ሱሰኞች ሊሆኑ ይችላሉ። በተጨማሪም ልጆች የጉልበት ሥራ እየሰሩ ትምህርት ቤት ለመከታተል የማይችሉ ከመሆናቸውም በላይ ሌሊት ለረጅም ሰዓት ይሰራሉ።